# ትንቢተ ፡ ናሖም ።

(ክለሳ.1.20020507)

__________________ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ ስለ ፡ ነነዌ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፤ የኤልቆሻዊው ፡ የናሖም ፡ የራእዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛና ፡ ተበቃይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ተበቃይና ፡ መዓትን ፡ የተሞላ ፡
ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ይበቀላል ፥ ለጠላቶቹም ፡ ቍጣውን ፡ ይጠብቃል ።

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ትዕግሥተኛ ፥ ኀይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ በደለኛውንም ፡— ንጹሕ ፡ ነኽ ፡ አይልም ፤ እግዚአብሔር ፡
በወጀብና ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ አለው ፥ ደመናም ፡ የእግሩ ፡ ትቢያ ፡ ነው ።

4 ፤ ባሕሩንም ፡ ይገሥጻታል ፥ ያደርቃትማል ፥ ወንዞችንም ፡ ዅሉ ፡ ያደርቃል ፤ ባሳንና ፡ ቀርሜሎስም ፡
ላልተዋል ፥ የሊባኖስም ፡ አበባ ፡ ጠውልጓል ።

5 ፤ ተራራዎችም ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ ታወኩ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ቀለጡ ፤ ምድርና ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩበትም ፡ ዅሉ ፡ ከፊቱ ፡
ተናወጡ ።

6 ፤ በቍጣው ፡ ፊት ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ የቍጣውንም ፡ ትኵሳት ፡ ማን ፡ ይታገሣል ፡፡ መዓቱ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡
ይፈሳል ፥ ከርሱም ፡ የተነሣ ፡ አለቶች ፡ ተሰነጠቁ ።

7 ፤ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ ነው ፥ በመከራ ፡ ቀንም ፡ መሸሸጊያ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ የሚታመኑትንም ፡ ያውቃል ።

8 ፤ ስፍራዋን ፡ ግን ፡ በሚያጥለቀልቅ ፡ ጐርፍ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋታል ፥ ጠላቶቹንም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ያሳድዳቸዋል ።

9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የምታስቡት ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋል ፥ መከራም ፡ ኹለተኛ ፡ አይነሣም ።

10 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንደ ፡ ተመሰቃቀለ ፡ ሾኽ ፡ ቢኾኑ ፥ በመጠጣቸውም ፡ ቢሰክሩ ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ገለባ ፡
ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ።

11 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ የሚያስብ ፥ ክፋትን ፡ የሚመክር ፥ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቷል ።

12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡— ኀይለኛዎችና ፡ ብዙዎች ፡ ቢኾኑ ፡ እንዲሁ ፡ ይቈረጣሉ ፥ ርሱም ፡
ያልቃል ። እኔም ፡ አስጨንቄኻለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስጨንቅኽም ።

13 ፤ አኹንም ፡ ቀንበሩን ፡ ከአንተ ፡ እሰብራለኹ ፥ እስራትኽንም ፡ እበጥሳለኹ ።

14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከስምኽ ፡ ማንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይዘራ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ አዟል ፤ ከአምላኮችኽ ፡ ቤት ፡
የተቀረጸውንና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስል ፡ አጠፋለኹ ፤ አንተም ፡ የተጠቃኽ ፡ ነኽና ፥ መቃብርኽን ፡ እምሳለኹ ።

15 ፤ እንሆ ፥ የምሥራችን ፡ የሚያመጣ ፡ ሰላምንም ፡ የሚያወራ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ነው! ይሁዳ ፡
ሆይ ፥ አጥፊው ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፍቷልና ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አያልፍምና ፡ ዓመት ፡ በዓሎችኽን ፡
አድርግ ፥ ስእለቶችኽን ፡ ክፈል ።

__________________ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ የሚቀጠቅጥ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ወጥቷል ፤ ምሽግን ፡ ጠብቅ ፥ መንገድንም ፡ ሰልል ፤ ወገብኽን ፡ አጽና ፥ ኀይልኽንም ፡
እጅግ ፡ አበርታ ።

2 ፤ ዘራፊዎች ፡ ዘርፈዋቸዋልና ፥ የወይናቸውንም ፡ ዐረግ ፡ አጥፍተዋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ የያዕቆብን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡
እስራኤል ፡ ክብር ፡ ይመልሳል ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ የኀያላኑ ፡ ጋሻ ፡ ቀልቷል ፥ ጽኑዓንም ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ። ርሱም ፡ በሚያዘጋጅበት ፡ ቀን ፡ ሠረገላዎች ፡
እንደ ፡ እሳት ፡ ይንቦገቦጋሉ ፤ የጦሩም ፡ ሰማያ ፡ ይወዛወዛል ።

4 ፤ ሠረገላዎች ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ይነጕዳሉ ፥ አደባባይም ፡ ይጋጫሉ ፤ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ነው ፥ እንደ ፡
መብረቅም ፡ ይከንፋሉ ።

5 ፤ መሳፍንቱን ፡ ያስባል ፤ በአረማመዳቸው ፡ ይሰናከላሉ ፤ ፈጥነው ፡ በቅጥሯ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፥ መጠጊያም ፡
ተዘጋጀለት ።

6 ፤ የወንዞቹም ፡ መዝጊያዎች ፡ ተከፈቱ ፥ የንጉሡ ፡ ቤትም ፡ ቀለጠች ።

7 ፤ ንግሥት ፡ ተገለጠች ፥ ተማረከችም ፥ ሴቶች ፡ ባሪያዎቿም ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ እየጮኹና ፡ ደረታቸውን ፡ እየመቱ ፡
ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ።

8 ፤ ነነዌ ፡ ግን ፡ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ ዠምራ ፡ እንደ ፡ ተከማቸ ፡ ውሃ ፡ ነበረች ፤ አኹን ፡ ግን ፡
ይሸሻሉ ፤ እነርሱም ፦ ቁሙ ፥ ቁሙ ፡ ይላሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የሚመለስ ፡ የለም ።

9 ፤ መዝገቧ ፡ መጨረሻ ፡ የለውምና ፥ የከበረውም ፡ የዕቃዋ ፡ ኹሉ ፡ ብዛት ፡ አይቈጠርምና ፡ ብሩን ፡
በዝብዙ ፥ ወርቁንም ፡ በዝብዙ ።

10 ፤ ባዶና ፡ ባድማ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ኾናለች ፤ ልብ ፡ ቀልጧል ፥ ጕልበቶችም ፡ ተብረክርከዋል ፤ በወገብም ፡ ኹሉ ፡
ሕማም ፡ አለ ፥ የሰዎችም ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ጠቍሯል ።

11 ፤ የአንበሳዎችም ፡ መደብ ፥ የአንበሳዎችም ፡ ደቦል ፡ የሚሰማራበት ፥ አንበሳውና ፡ አንበሳዪቱ ፡ ግልገሉም ፡ ሳይፈሩ ፡
የሚኼዱት ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

12 ፤ አንበሳው ፡ ለልጆቹ ፡ የሚበቃውን ፡ ነጠቀ ፥ ለእንስቶቹም ፡ ሰበረላቸው ፡ ዋሻውን ፡ በንጥቂያ ፥ መደቡንም ፡
በቅሚያ ፡ ሞልቶታል ።

13 ፤ እንሆ ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ሠረገላዎቿንም ፡ አቃጥዬ ፡
አጤሳለኹ ፥ ሰይፍም ፡ የአንበሳ ፡ ደቦሎችሽን ፡ ይበላቸዋል ፤ ንጥቂያሽንም ፡ ከምድር ፡ አጠፋለኹ ፥ የመልክተኛዎችሽን ፡
ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሰማም ።

## ትንቢተ ፡ ናሑም ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ለደም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት! በኹለንተናዋ ፡ ሐሰትና ፡ ቅሚያ ፡ ሞልቶባታል ፤ ንጥቂያ ፡ ከርሷ ፡ አያልቅም ።

2 ፤ የዐለንጋ ፡ ድምፅ ፥ የመንኰራኵርም ፡ ድምፅ ፥ የፈረሶችም ፡ ኰቴ ፥ የፈጣን ፡ ሠረገላም ፡ ጩኸት ፡ ተሰምቷል ፤

3 ፤ ፈረሰኛው ፡ ይጋልባል ፥ ሰይፍም ፡ ይንቦገቦጋል ፥ ጦርም ፡ ይብለጨለጫል ፤ የተገደሉትም ፡ ይበዛሉ ፥ በድኖችም ፡
በክምር ፡ ይከመራሉ ፥ ሬሳቸውም ፡ አይቈጠርም ፤ በሬሳቸውም ፡ ይሰናከላሉ ።

4 ፤ ስለተዋበችው ፡ ጋለሞታ ፡ ግልሙትና ፡ ብዛት ፡ ይህ ፡ ኾኗል ፤ ርሷም ፡ በመተቷ ፡ እጅግ ፡ በለጠች ፥ አሕዛብንም ፡
በግልሙትናዋ ፥ ወገኖችንም ፡ በመተቷ ፡ ሸጠች ።

5 ፤ እንሆ ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ልብስሽን ፡ በፊትሽ ፡ እገልጣለኹ ፤ ኀፍረተ ፡
ሥጋሽንም ፡ ለአሕዛብ ፥ ነውርሽንም ፡ ለመንግሥታት ፡ አሳያለኹ ።

6 ፤ ርኵሰትንም ፡ በላይሽ ፡ እጥላለኹ ፥ እንቅሽማለኹ ፥ ማላገጫም ፡ አደርግሻለኹ ።

7 ፤ የሚያይሽም ፡ ኹሉ ፡ ከአንቺ ፡ ሸሽቶ ፦ ነነዌ ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፤ የሚያለቅስላትስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚያጽናናትንስ ፡
ከወዴት ፡ እፈልጋለኹ ፧ ይላል ።

8 ፤ አንቺ ፡ በመስኖች ፡ መካከል ፡ ከተቀመጠችው ፥ ውሃም ፡ በዙሪያዋ ፡ ከነበራት ፥ ምሽጓም ፡ ባሕር ፡
ከነበረ ፥ ቅጥሯም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ከነበረ ፡ ከኖእ ፡ ዐሞን ፡ ትበልጫለሽን ፧



www.ethiopianorthodox.org

9 ፤ ኢትዮጵያና ፡ ግብጽ ፡ የማይቈጠር ፡ ኀይሏ ፡ ነበሩ ፤ ፉጥና ፡ ልብያ ፡ ረዳቶቿ ፡ ነበሩ ።

10 ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ ተማርካ ፡ ፈለሰች ፤ ሕፃናቷ ፡ በመንገድ ፡ ዅሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተፈጠፈጡ ፤ በከበርቴዎቿም ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡
ተጣጣሉ ፣ ታላላቆቿም ፡ ዅሉ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሰሩ ።

11 ፤ አንቺም ፡ ትሰክሪያለሽ ፡ ወራዳም ፡ ትኾኛለሽ ፤ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ከጠላት ፡ የተነሣ ፡ መጠጊያን ፡ ትፈልጊያለሽ ።

12 ፤ ዐምባሽ ፡ ዅሉ ፡ የመዠመሪያውን ፡ የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ እንደ ፡ በለስ ፡ ዛፎች ፡ ነው ፤ ቢወዛወዝ ፡
በሚበላው ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃል ።

13 ፤ እንሆ ፣ በመካከልሽ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብሽ ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ፤ የአገርሽ ፡ በሮች ፡ ለጠላቶችሽ ፡ ፈጽሞ ፡
ተከፍተዋል ፣ እሳትም ፡ መወርወሪያዎችኽን ፡ በልቷል ።

14 ፤ ከበው ፡ ያስጨንቁሻልና ፣ ውሃን ፡ ቅጂ ፤ ዐምባሽን ፡ አጠንክሪ ፤ ወደ ፡ ጭቃ ፡ ገብተሽ ፡ ርገጪ ፤ የጡብን ፡
መሠሪያ ፡ ያዢ ።

15 ፤ በዚያ ፡ እሳት ፡ ይበላሻል ፣ ሰይፍ ፡ ያጠፋሻል ፣ እንደ ፡ ደጐብያ ፡ ይበላሻል ፤ እንደ ፡ ደጐብያ ፡ ብዢ ፣ እንደ ፡
አንበጣም ፡ ተባዢ ።

16 ፤ ነጋዴዎችሽን ፡ ከሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ይልቅ ፡ አበዛሽ ፤ ደጐብያ ፡ ተዘረጋ ፣ በረረም ።

17 ፤ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ዘውድ ፡ የጫኑት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፣ አለቃዎችሽም ፡ እንደሚንቀሳቀሱ ፡ ኵብኵባዎች ፡
ናቸው ፤ በብርድ ፡ ቀን ፡ በቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ፣ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ያኰበኵባሉ ፤ ስፍራቸው ፡ በየት ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ አይታወቅም ።

18 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፣ እረኛዎችኽ ፡ አንቀላፍተዋል ፤ መኳንንቶችኽም ፡ ዐርፈዋል ፤ ሕዝብኽም ፡ በተራራዎች ፡
ላይ ፡ ተበትኗል ፣ የሚሰበስበውም ፡ የለም ።

19 ፤ ስብራትኽ ፡ አይፈወስም ፣ ቍስልኽም ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ወሬኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ዅሉ ፡ እጃቸውን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡
ያጨበጭባሉ ፤ ክፋትኽ ፡ ዅልጊዜ ፡ ያላለፈችበት ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነውና ❖



www.ethiopianorthodox.org